የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

## OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 17ኛ ዓመት ቁጥር 5<br>17th Year No. 5 | | ሐረር ታህሳስ 17/2004 ዓ/ም<br>HARAR, Dec. 27/2011 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 4.50<br>Unit Price Birr 4.50 | በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖ.ሣ.ቁ. 272<br>P.O.Box 272 |


ማውጫ

ደንብ ቁጥር 46/2004 ዓ/ም

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የገቢ ታሪፍን ለማሻሻል ወጣ ........................ገጽ 596

## ደንብ ቁጥር 46/2004 ዓ./ም

## የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የገቢ ታሪፍን ለማሻሻል የወጣ ደንብ

የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የገቢ ታሪፍን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 28/2001 ዓ/ምን ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በሐረር ከተማ አዋጅ ቁጥር 58/1998 አንቀፅ 36 (1) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### 1 አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት የገቢ ታሪፍ 1ኛ ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 46/2004 ዓ/ም›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ማሻሻያ

የሐረሪ ህዝብ ክልል የማዘጋጃ ቤት የገቢ ታሪፍን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 28/2001 ዓ/ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

1. አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 2 ተተክቷል፤
2. 2/ በክልሉ ከተማ የሐይማኖት ተቋማት፣ የህዝባዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ (ረድኤት) ድርጅቶች በስተቀር ሌሎች ማንኛውም መንግስታዊ መ/ቤቶች፣የህክምና ተቋማት እና ድርጅቶች፣ የግል መኖሪያ ቤቶች ተከራይ፣ የቀበሌ መኖሪያ ቤት፣ የግለሰብ መኖሪያ ቤት እና የመንግሥት መኖሪያ ቤትና ቁጠባ ቤት ተከራዮች የከተማ ፅዳት አገልግሎት ክፍያ ይፈፅማሉ፡፡
2. አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 2 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 3 እና 4 ተጨምሯል፡፡

   ”3 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ የፅዳት አገልግሎት ክፍያው በከተማ መግቢያ በሮች የሚከፈል የፅዳት አገልግሎትን፣ የሙት እንስሳት ለማስወገድ የሚከፈል የፅዳት

አገልግሎትን ያጠቃልላል፡፡››

”4. በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሱት እንደተጠበቀ ሆኖ ከደንብ ቁጥር 28/2001 ጋር ተያይዞ የሚገኘው ሰንጠረዥ 3 ቀጥሎ አዲስ የሰንጠረዥ 3 አካል የሆነ ከተማ ቦታ ኪራይ ተመን ክፍያን የሚያመለክቱ ሰንጠረዥ 3.1 እና 3.2 ተጨምሯል”

3. ከደንቡ ቁጥር 28/2001 ጋር ተያይዞ የሚገኘው ሰንጠረዥ 2 በተራ ቁጥር 2 ንዑስ ቁጥር 9 ቀጥሎ አዲስ ተራ ቁጥር 2 ንዑስ ቁጥር 10 ሰንጠረዥ 2 ተጨምሯል፡፡

**3. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሐረር ታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ/ም**

**ሙራድ አብዱልሃዲ**

**የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት**

**ፕሬዝዳንት**

## ሰንጠረዥ 3.1

## የግል መኖሪያ ቤት ነባር ቦታ ኪራይ ክፍያ ተመን ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የቦታ ስፋት በካሬ ሜትር | የቦታ ኪራይ ተመን /ብር በካሬ ሜትር/ በዓመት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ደረጃ | 2ና ደረጃ | 3ኛ ደረጃ |
| 1 | እስከ 200 | 0.29 | 0.25 | 0.21 |
| 2 | ከ201-300 | 0.31 | 0.27 | 0.23 |
| 3 | 301-400 | 0.34 | 0.29 | 0.25 |
| 4 | ከ401-500 | 0.39 | 0.33 | 0.29 |
| 5 | ከ500 በላይ | 0.46 | 0.39 | 0.35 |

## ሰንጠረዥ 3.2

## ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ ለማህበራዊ አገልግሎት፣ የሚከራይ መኖሪያ ቤት፣ ለአፓርታማ አገልግሎት ነባር ቦታ ኪራይ ክፍያ ተመን ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የቦታ ደረጃ | የቦታ ኪራይ ዋጋ በአገልግሎት ዓይነት/ ብር በካሬ ሜትር / በዓመት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ንግድ | ኢንዱስትሪ | ማህበራዊ አገ/ት | የሚከራይ መኖሪያ ቤት | አፓርታማ |
| 1 | 1ኛ | 1.88 | 1.00 | 1.05 | 0.52 | 0.78 |
| 2 | 2ኛ | 1.54 | 0.82 | 0.84 | 0.41 | 0.69 |
| 3 | 3ኛ | 1.25 | 0.60 | 0.64 | 0.31 | 0.61 |

## ሰንጠረዥ 2

| ተ.ቁ | የገቢ ርዕስ | ደረጃ (መስፈርት) | ተመን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ብር | ሣ |
| 2.10 | የፅዳት አገልግሎት ክፍያ (ቆሻሻን ማስወገጃ) | | | |
| ሀ | ለመንግስታዊ ሆስፒታል | በዓመት | 1200 | 00 |
| ለ | በከተማው የሚገኝ ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት | በዓመት | 500 | 00 |
| ሐ | ለግል መኖሪያ ቤት በተያዘ የቦታ ስፋት መጠን ሆኖ | | | |
| | 1. እስከ 300 ሜ.ካ | በወር | 3 | 00 |
| | 2. 301 እስከ 500 ሜ.ካ | በወር | 5 | 00 |
| | 3. 501 ሜ.ካ በላይ | በወር | 7 | 00 |
| መ | ለቀበሌ መኖሪያ ቤት ተከራይ | በወር | 3 | 00 |
| ሠ | የመንግስት መኖሪያ ቤት ወይም ቁጠባ ቤት ተከራይ፤ | በወር | 5 | 00 |
| ረ | የግለሰብ መኖሪያ ቤት ተከራይ በቤት ኪራይ ተመን መነሻ የሚከፈል ሆኖ በአከራዩ እየተሰበሰበ ገቢ የሚደረግ ፤ | | | |
| | 1. ከብር 100 በታች ለሚከራይ ቤት | በወር | 3 | 00 |
| | 2. ከብር 100-200 ለሚከራይ ቤት | በወር | 5 | 00 |
| | 3. ከብር 201-500 ለሚከራይ ቤት | በወር | 7 | 00 |
| | 4. ከብር 500 በላይ ለሚከራይ ቤት | በወር | 10 | 00 |
| ሸ | በከተማ መግቢያ በሮች ሲገቡ የሚከፈል | | | |
| | 1. የዳልጋ ከብት ግመልና የጋማ ከብት፤ | በከብት ቁጥር | 5 | 00 |
| | 2. በግ፣ ፍየልና አሳማ፤ | በእንስሳት ቁጥር | 1 | 00 |
| | 3. ነጭና ቀይ አሸዋ፤ | በመኪና | 15 | 00 |
| | 4. ድንጋይና ጠጠር እና ሌሎች | በመኪና | 20 | 00 |
| ቀ | የሙት እንስሳትን ለማስወገድ የሚከፈል (ያላሳወቀ ሰው ያሳወቀው ከሚከፍለው ክፍያ እጥፍ ይከፍላል) | | | |
| | 1. ለአህያ ለፈረስ ፣ ለመቅሎ፣ ለላም፣ ለበሬ፣ ለግመል፣ በህጋዊ መንገድ ላሳወቀ | በእንስሳት ቁጥር | 30 | 00 |
| | 2. ለጥጃ በህጋዊ መንገድ ላሳወቀ፤ | በቁጥር | 15 | 00 |
| | 3. ለበግ፣ ለፍየል፣ ለአሳማ፣ ለውሻ፣ በህጋዊ መንገድ ላሳወቀ | በቁጥር | 10 | 00 |